# የደህንነት እቅድ



## የደህንነት እቅድ ምንድን ነው?

**የደህንነት እቅድ*** እግዚአብሔር ለልጆቹ ደህናነት ያለው እቅድ ነው። ይህም በኢየሱስ ክርስቶስ **የኃጢያት ክፍያ** ላይ የተመሰረተ ነው። የኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርቶችን ከተከተላችሁ፣ በእዚህ ህይወት የማይጠፉ ውስጣዊ ሰላም እናም ከሞት በኋላ የዘለአለም ደስታን ታገኛላችሁ።

ስለደህንነት እቅድ ስትማሩ፣ ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ታገኛላችሁ፥ "ከየት ነው የመጣሁት?" "የህይወቴ እቅድ ምንድን ነው?" "ከእዚህ ህይወት በኋላ የት እሄዳለሁ?"

## ከየት ነው የመጣሁት?

ህይወትህ በምትወለድበት አልተጀመረም፣ ወይም በሞት ላይ አያል ቅም። (አንዳንዴ ነፍስ ተብሎ በሚጠራው) **በመንፈስ** ሰውነት እና በስጋዊ ሰውነት የተሰራችሁ ናችሁ። የሰማይ አባት መንፈሳችሁን ፈጥሯል፣ እናም በምድር ላይ ከመወለዳ ችሁ በፊት ከእርሱ ጋር ትኖሩ ነበር። እርሱን ትውቁ እና ታፈቅሩ ነበር፣ እና እርሱም ያውቃችሁና ያፈቅራችሁ ነበር። ይህም ጊዜ **ቅድመ ምድራዊ ህይወት** ተብሎ ይጠራል።

> *"የደህንነት ዕቅድ ከዓለም መፈጠር ጀምሮ፣ በክርስቶስ በኩል፣ በስሙ ለሚያምኑ ሁሉ የተዘጋጀውን ነው።]"*
>
> አልማ 22፥13

በቅድመ ምድራዊ ህይወታችሁ፣ ወደ ደስታ ስለሚመሩት መሰረታዊ መርሆች እና ትእዛዛት ተምራችኋል። በእውቀት አደጋችሁ እና እውነትን ለመውደድ ተማራችሁ። ስለደህንነት እቅድ ተምራችሁም ነበር። በእዚህ ቅድመ ምድራዊ ህይወት፣ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ አዳኝ ተመርጦ ነበር፤ በእርሱም የመጥፎ ምርጫችሁን ውጤት ለማሸነፍ እንደምትችሉም ተማራችሁ።

የእግዚአብሔር እቅድ ዋና ክፍልም እናንተ ስጋዊ ሰውነትን እንድትቀበሉ እና ትክክለኛ ምርጫዎችን ለማድረግ እንድትማሩ ዘንድ ወደ ምድር እንድትመጡነበር። በሰማይ አባት ፊት መኖራችሁን አታስታውሱም፣

* በቀይ ቀለም ያሉት ቃላት በገጾች 18 እና 19 ውስጥ ተገልጸዋል።




3

ነገር ግን ትክክል የሆኑትን ትክክል ካልሆኑት ለይቶ ለማወቅ ችሎታ ይሰጣችኋል። ፍቅሩን እና እውነቱን ለማወቅ ትችላላችሁ። በሚያጋጥማ ችሁ እና በፈተናዎቻችሁ፣ ትክክለኛ ምርጫዎችን ሁልጊዜ ለመስራት ለመማር ትችላላችሁ። በኢየሱስ ክርስቶስ እርዳታ፣ የምድር ህይወታችሁ ሲፈጸም ከሰማይ አባት ጋር ለመኖር ለመመለስ ትችላላችሁ።

*ምንም እንኳን ስለእዚህ ያላችሁ ትዝታ የተገደበ ቢሆንም፣ ወደ እዚህ ምድር ከመምጣታችሁ በፊት የዘለአለም አባታችሁ ከሆነው እግዚአብሔር እና ከልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ትኖሩ ነበር። ወደ እዚህ ምድር ሰውነትን ለመቀበል እና የእግዚአብሔርን የደስታ እቅድ ለመከተል ለመምጣት ላላችሁ እድል በደስታ ጮሀችሁ።*

በቅድመ-ምድር ህይወታችሁ፣ የማይጠፋ ሰላም እና እርካታ በእዚህ ህይወት እና በዘለአለም ለመቀበል የምትችሉት የእግዚአብሔርን እቅድ በመከተል ብቻ እንደሆነ ተማራችሁ። ስለሚያፈቅራችሁ፣ የሰማይ አባት **ነጻ ምርጫ**፣ ወይም የመምረጥ ሀይል፣ ሰጥቷችኋል። የእርሱን እቅድ እና ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ለመከተል ወል ላለመከተል እንድትመርጡም ይፈቅድላችኋል።

ከእግዚአብሔር የመንፈስ ልጆች አንዱ የሆነው ሰይጣን በሰማይ አባት ላይ አመጸ እናም እቅዱን አልተቀበለም። ሁላችንም የእርሱን ፍላጎት እንድና ደርግ ፈለገ። በሚያሳዝን ሁኔታም፣ ብዙዎቹ የሰማይ አባት ልጆች ሰይጣንን ለመከተል መረጡ። ሰይጣን እና ተከታዮቹ ከእግዚአብሔር ፊት ተወገዱ እናም በምድር ላይ እንዲወለዱም አልተፈቀደላቸውም። እንደ መንፈስ መኖርም ቀጠሉ። እነርሱም የተከፉ ናቸው፣ እናም እናንተ የተከፋችሁ እንድትሆኑ ይፈልጋሉ። እናንተ እና የእግዚአብሔር ልጆች በሙሉ ሀዘንን የሚያመጡ እና እግዚአብሔርን የማያስደስቱ ነገሮችን እንዲያደርጉ ይፈትኗሉ።

በቅድመ-ምድር ህይወት ውስጥ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ለማመን እና የእግዚአብሔርን እቅድ ለመከተል መረጣችሁ። በምርጫችሁ ምክንያት፣ መብድር ላይ ተወልዳችሁ ነበር። በእዚህ ህይወት ሰላም እና ከእዚህ ህይወት በኋላ ከሰማይ አባት ጋር ለመኖር የምትችሉት እንደ እነዚህ አይነት ምርጫዎችን በማድረግ ብቻ ነው።

በቀይ ቀለም ያሉት ቃላት በገጾች 18 እና 19 ውስጥ ተገልጸዋል።

*በእዚህ ህይወት ለመማር እና ሊያጋጥመን የምንችል ብዙ ነገሮች አሉ።*

# የህይወታችሁ እቅድ ምንድን ነው?

## ፍጥረት እና ውድቀት

አለም የተፈጠረችው የሰማይ አባት ልጆች እንደሚኖሩበት እና አጋጣሚ ዎች እንደሚያገኙበት ቦታ ነበር። አዳም እና ሔዋን ወደ ምድር ከመጡት የእግዚአብሔር ልጆች የመጀመሪያ ነበሩ። በእግዚአብሔር ፊት ይገኙበት በነበረበት የዔደን ገነት ተብሎ በተጠራው ቦታ ውስጥ ኖሩ።

የሰማይ አባት ለአዳም እና ሔዋን ነጻ ምርጫ፣ ወይም የመረጥ ልነጻነት ሰጣችሁ። የመልካም እና ክፉ እውቀት ዛፍ ፍሬን እንዳይበሩ ትእዛዝ ሰጣቸው። ይህን ትእዛዝ ምክበር በገነት ለመቆየት ይችላሉ ማለት ነበር፣ ነገር ግን በአጋጣሚዎችና በፈተናዎች በመማር ለማደግ አይችሉም ነበር። ሰይጣን አዳም እና ሔዋን የተከለከሉትን ፍሬ እንዲበሉ ፈተናቸው፣ እናም እነርሱም ይህን አደረጉ። ይህም የእግዚአብሔር እቅድ ክፍል ነበር። በውሳኔአቸው ምክንያት፣ ከእግዚአብሔር ፊት በስጋዊ እና በመንፈሳዊ ሁኔታ ተለይረው ነበር። ሟች፣ ይህም ማለት ለኃጢያት እና ለሞት ተገዢ፣ ሆኑ። ወደ እርሱ ያለእርዳታ ለመመለስ አይችሉም ነበር። ከእግዚአብሔር በስጋዊ እና በመንፈሳዊ ሁኔታ መለየታቸው ውድቀት ተብሎ ይጠራል።

አዳምን እና ሔዋንን ስለደህንነት እቅድ ለማስተማር የሰማይ አባት መላእክትን እና መንፈስ ቅዱስን ላከ። የእቅዱ ዋና ክፍልም የኢየሱስ ክርስቶስ የኃጢያት ክፍያ ነው፣ ይህም የእግዚአብሔር ልጆች የውድቀትን ውጤት ለማሸነፍ እና በእዚህ ህይወት እና በዘለአለም ውስጥ ደስታን ለማግኘት የሚያስችል ነው።

በቀይ ቀለም ያሉት ቃላት በገጾች 18 እና 19 ውስጥ ተገልጸዋል።

"አዳም ባይተላለፍ ኖሮ አይወድቅም ነበር፣ ነገር ግን በዔድን ገነት ይቆይ ነበር። . . .

"እናም [አዳም እና ሔዋን] ልጆች አይኖራቸውም ነበር፤ ስለዚህ በየዋህነት ይቆዩ ነበር፣ ደስታ አይኖራቸውም፣ መከራንም አያውቁምና፤ ኃጢያትን ባለማወቃቸው መልካምን አይሰሩም።

"ነገር ግን እነሆ፣ ሁሉም ነገሮች የተደረጉት ሁሉንም ነገሮች በሚያውቀው በጌታ ጥበብ ነው።

"ሰዎች እንዲኖሩ፣ አዳም ወደቀ፤ እና ሰዎች የሚኖሩትም ደስታ እንዲኖራቸው ዘንድ ነው።"

2 ኔፊ 2፥22–25



## የምድር ህይወታችሁ

በውድቀት ምክንያት፣ ከእግዚአብሔር ጋር በስጋዊ እና በመንፈሳዊ ሁኔታ ተለያይታችኋል። ይህም መለያየት እግዚአብሔር ለልጆቹ ያለው እቅድ ክፍል ነው። ከእርሱ ፊት ወጥታችሁ ወደ ምድር የምመጣታችሁ እቅድ በተጨማሪ ሰውነትን ለማግኘት፣ አጋጣሚዎ ችን ለማግኘት፣ እና በትክክል ምርጫዎች ለመማር ነው።

የህይወት ብዙ ሁኔታዎች ደስታን ያመጣሉ፣ እናም አንዳንዶችም ሀዘንን ያመጣሉ። እነዚህ አጋጣሚዎች በመልካም እና በክፉ መካከል ልዩነትን ለማወቅ እንድትማሩ እና ትክክለኛ ምርጫዎችን እንድታደርጉ እርዳታ ይሰጣች ኋል። እግዚአብሔር መልካም እንድታደርጉ እና እርሱን እንድትከተሉ እናንተ ላይ ተፅዕኖ አለው፣ ሰይጣንም እግዚአብሔርን ችላ እንድትሉ እና ኃጢያትን እንድትሰሩ ይፈትናችኋል። (ኃጢያት ትክክል ያልሆነ ውን ለማድረግ መምረጥ ወይም ትክክል የሆነውን አለማድረግ ነው።) እግዚአብሔርን ለመከተል እና ትእዛዛቱን ለመከተል ስትመርጡ፣ በጥበብ እና በጸባይ ጥንካሬ ታድጋላችሁ። በፈተና ጊዜዎች ደስታ ሊያጋጥማችሁ ትችላላችሁ፣ እናም የህይወት ፈተናዎችን በሰላም መንፈስ ለመቋቋም ትችላላችሁ።

> *"እኔ የእግዚአብሔ ልጅ ነኝ፣*
> *ወደ እዚህም ላከኝ፣*
> *ከደግ እና ውድ ቤተሰብ*
> *ጋር ምድራዊ ቤት ሰጠኝ*
> *ምራኝ፣ ጠብቀኝ፣ ተከተለኝ፣*
> *መንገዱን እንዳውቅ እርዳኝ።*
> *ከእርሱ ጋር አንድ ቀን ለመኖር*
> *ማድረግ ያለብኝን ልማር።"*
>
> Hymns፣ ቁጥር 223።

በህይወታችሁ ብዙ ጥሩ ምርጫዎች ሰርታችኋል፣ ነገር ግን ብዙ ትክክል ያልሆነ ምርጫዎችንም አድርጋችኋል። ትክክል ያልሆነ ምርጫዎችን ስታደርጉ እና ኃጢያቶችን ስትሰሩ፣ ከእግዚአብሔር እራሳችሁን በደረጃ ትለያላችሁ። በቅዱሳት መጻህፍት ውስጥ ይህ መለያየት **የመንፈስ ሞት ተብሎ ይጠራል።** ከእግዚአብሔር ከመለየት በተጨማሪም፣ ኃጢያት ጥፋተኛነት እና እፍረትን ያመጣል። ኃጢያትን እና ውጤቱን በብቻችሁ ለማሸነፍ አትችሉም።

በቀይ ቀለም ያሉት ቃላት በገጾች 18 እና 19 ውስጥ ተገልጸዋል።

## የኢየሱስ ክርስቶስ የኃጢያት ክፍያ

የሰማይ አባት ስለሚያፈቅራችሁ፣ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስ ለኃጢያቶቻችሁ እንዲከፍል ልኳል። ይህም ክፍያ የኢየሱስ ክርስቶስ የኃቲያት ክፍያ ክፍል ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ለኃቲያቶቻችሁ፣ ለጉዳታችሁ፣ ለበሽታችሁ፣ እና ለሀዘናችሁ በፈቃደኛነት ተሰቃይቷል። በእርሱ ጸጋ እና ምህረት በኩል፣ በፈተናችሁ ሊረዳችሁና የኃቲያቶቻችሁ ውጤት ከሆኑት ጥፋተኛነት እና እፍረት ሊያሳርፉችሁ ይችላል።

> *"በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአል።"*
>
> ዮሀንስ 3፥5

ለኃጢአያታችሁ በመክፈል፣ ኢየሱስ የእናንተን ነጻ ምርጫ ወይም ሀላፊነት አላስወገደም—ያለፈቃዳችሁ ንጹህ አያደርጋችሁም። የእርሱን እርዳታ እና ጥንካሬ ለመቀበል፣ በእርሱ ማመን፣ ንስሀ መግባት፣ መጠመቅ፣ መንደስ ቅዱስን መቀበል፣ እና የእርሱን ትምህርት በህይወታችሁ ሁሉ ለመከተል መምረጥ ያስፈልጋችኋል። በኃጢያት ክፍያ ላይ ስትመኩ፣ የእግዚአብሔር ፍቅር ይሰማችኋል፣ እናም ፈተናዎቻችሁን እንድትፅናኑ ይረዳችኋል። ደስታ፣ ሰላም፣ እና መፅናናትም ያጋጥማችኋል። በህይወት ሚዛናዊ ያልሆኑ የሚመስሉት ሁሉም ነገሮች በኢየሱስ ክርስቶስ የኃጢያት ክፍያ እና በሰማይ አባት ምህረት እና ፍቅር በኩል ትክክል ለማድረግ ይቻላል። የኃጢያት ክፍያ የደህንነት እቅድ ዋና ነጥብ ነው።

## ከእዚህ ህይወት በኋላ የት እሄዳለሁ?

ከምድራዊ አስተያየት፣ ስጋዊ ሞት መጨረሻ እንደሆነ ይመስላል፣ ነገር ግን ይህ መጀመሪያ፣ በሰማይ አባት እቅድ ወደ ፊት የሚገፉበት እርምጃ ነው። በሞት ጊዜ፣ መንፈሳችሁ ከሰውነታችሁ ይለያል እናም የመማሪያ እና የመዘጋጃ ቦታ ወደሆነው መንፈስ አለም አለም ይሄዳል። በመንፈስ አለም ውስጥ፣ የህይወታችሁ ትዝታ ከእናንተ ጋር ይገኛል።

በቀይ ቀለም ያሉት ቃላት በገጾች 18 እና 19 ውስጥ ተገልጸዋል።



*በሞት ጊዜ መንፈሳችሁ ከሰውነታችሁ ይለያል እናም የመዘጋጃ፣ የመማሪያ እና ከጭንቀት እና ከሀሰን ማረፊያ ወደሆነው ወደ መንፈስ አለም ይሄዳል።*

ሞት የግል ጸባያችሁን ወይም ለመልካምም ሆነ ለክፉ ያላችሁን ፍላጎት አይቀይርም። በምድር ህይወታችሁ ክርስቶስን ለመከተል ከመረጣችሁ፣ በመንፈስ ሰላም ውስጥ ሰላም ይኖራችኋል እናም ከምትጨነቁበት ታርፋላችሁ። ኢየሱስ ክርስቶስን ላለመከተል የመረጡት እና ንስሀ የማገቡትም የተከፉ ይሆናሉ።

የሰማይ አባት ብዙዎቹ ልጆቹ በህይወታቸው ጊዜ ስለኢየሱስ ክርስቶስ ለመማር እድል እንደማይኖራቸው እና ሌሎችም እርሱን ለመከተል እንደማይመርጡ ያውቃል። ልጆቹን ስለሚያፈቅራቸው፣ እግዚአብሔር በመንፈስ አለም ውስጥ ላሉት የእርሱን እቅድ የሚማሩበት፣ በኢየሱስ ክርስቶስ እምነት የሚያገ/ኙበት፣ እና ንስሀ የሚገቡበት መንገድ አዘጋጀ። ኢየሱስ ክርስቶስን የተቀበሉ እና የሚከተሉም ሰላምና እፎርት ይኖራቸዋል።

## ትንሳኤ እና ፍርድ

ወደ ምድር ለመጡት እግዚአብሔር ከሰጣቸው ስጦታዎች መካከል ታላቅ የሆነው ትንሳኤ ነው፣ ይህም የሚቻለው በኢየሱስ ክርስቶስ የኃጢያት ክፍያ በኩል ነው። ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሲሞት፣ መንፈሱ ወደ መንፈስ አለም ሄደ። ከሶስት ቀናት በኋላ፣ መንፈሱ መሞት ከማይችለው ከግራዊ፣ ፍጹም ሰውነቱ ጋር በዳግም ተገናኘ። ይህ የመንፈስ ከሰውነት ጋር በዳግም መገናኘትም *ትንሳኤ ተብሎ ይጠራል*።በምድር ውስጥ የተወለደ ሁሉም ሰው በሞት ይነሳል።

ከሞት ከተነሳችሁ በኋላ፣ በእግዚአብሔር ፊት ሄዳችሁ በስራዎቻችሁ እና በልብ ፍላጎታችሁ መሰረት ይፈረድባችኋል።

በቀይ ቀለም ያሉት ቃላት በገጾች 18 እና 19 ውስጥ ተገልጸዋል።

*ከሞት የተነሳው አዳኝ በማርያም ታየ።*



## የክብር ደረጃ

ከተፈረደባችሁ በኋላ፣ በክብር ሁኔታ ትኖራላችሁ። የሁሉም ስራዎች እና ፍላጎቶች የተለያዩ ስለሆኑ፣ ሰማይ የተለያዩ መንግስቶች፣ ወይም የክብር ደረጃዎች፣ አሉት።

**የሰልስቲያል መንግስት።** የሰማይ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ በሰለስቲያል መንግስት ውስጥ ይኖራሉ። በኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል መሰረት ከኖራችሁ እና በኃጢያት ክፍያ ከኃጢያት ከተጸዳችሁ፣ እናንተ በእዚህ ከፍተኛው መንግስት በሆነው ውስጥ ቦታ ትቀበላላችሁ። በእግዚአብሔር ፊት ትኖራላችሁ እናም ሙሉ ደስታንም ታውቃላችሁ።

**ተረስትሪያል መንግስት።** የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ለመቀበል እምቢ ቢሉም የተከበረ ህይወት የኖሩት ሰዎች በተረስትሪያል መንግስት ውስጥ ቦታ ይቀበላሉ።

**ቲለስቲያል መንግስት።** በኃጢያት የሚቀጥሉት እና ንስሀ የማይገቡት በቲለስቲያል መንግስት ውስጥ ቦታ ይቀበላሉ።

**የኢየሱስ ክርስቶስ የኃጢያት ክፍያ ደህንነት እንዲገኝ ያደርጋል።**

**የቅድመ ምድር ህይወት**

ፍጥረት እና ውድቀት


**የምድር ህይወት**

በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን
ንስሀ መግባት
ጥምቀት
የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ
እስከመጨረሻ መፅናት

ስጋዊ ሞት

## እቅድ ለእኔ ምን ትርጉም አለው?

እግዚአብሔር የሰማይ አባታችሁ እንደሆነ፣ እንደሚያፈቅራችሁ፣ በእዚህ አጋጣሚን እና እውቀትን እንድታገኙ እናም ከእዚህ ህይወት በኋላ እንደ እርሱ ለመሆን እንድትችሉ እንዳደረገ ሲገባችሁ፣ በእዚህ ህይወት ውሳኔ የምታደርጉት ነገሮች አስፈላጊነት ታውቃላችሁ። የሰማይ አባት እቅዱን ሙሉ በረከቶች ለመቀበል ኢየሱስ ክርስቶስን መከተል እንዳለባችሁም ይገባችኋል።



## እንዴት ለማወቅ እችላለሁ?

**የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል በዳግም ስለተመለሰ ስለደህንነት እቅድ ታላቅ እውቀት መጥቷል።**

**እነዚህ ነገሮች እውነት እንደሆኑ የሰማይ አባትን በጸሎት በመጠየቅ ለእራሳችሁ ለማወቅ ትችላላችሁ። በመንፈስ ቅዱስ በኩል መልስ ይሰጣችኋል። መንፈስ ቅዱስ ደግሞም የእግዚአብሔር መንፈስ ተብሎ ይጠራል፣ እናም ከሃላፊነቶቹ አንዱ የእውነት ምስክርነት፣ ወይም ስለእውነት መመስከር ነው። መንፈስ ቅዱ እውነትን በስሜት፣ በሀሳቦች፣ እና በግንዛቤ በኩል ይገልጻል እናም ያረጋግጣል። ከመንፈስ ቅዱስ የሚመጡት ስሜቶች ሀይለኛ ናቸው፣ ነገር ግን በብዙ ጊዜ ረጋ ያሉ እና ጸጥተኛ ናቸው። በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደምን ማረው፣ "የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግሥት፥ ቸርነት፥ በጎነት፥ እምነት፥ የውሃት፥ ራስን መግዛት ነው" (ገላትያ 5:22–23)። እነዚህ ስሜቶች ይህ መልእክት እውነት እንደሆነ መንፈስ ቅዱስ የሚያረዳግጥባቸው ናቸው። ከእዚያም በጆሴፍ ስሚዝ በኩል በዳግም ከተመለሰው ከኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርት ጋር በስምም ነት ለመኖር መምረጥ ያስፈልጋችኋል።**

*እንዴት ለመጸለይ እችላለሁ?*

- *የሰማይ አባታችሁን በስሙ ጥሩ።*
- *የልብ ስሜታችሁን (ምስጋናን፣ ጥያቄዎችን፣ መፅሐፈ ሞርሞን እና የወንጌል መልእክተኞች ያስተማሯችሁ እውነት እንደሆኑ ማረጋገጫ መጠየቅን) ግለጹ።*
- *ጸሎትንም ዝጉ ("በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፣ አሜን")*

*እውነትን በልባዊ ጸሎት ለማወቅ ትችላላችሁ።*



## የስያሜዎች ዝርዝር

**መንፈሳዊ ሞት** ትእዛዛቱን ያለማክበር ውጤት የሆነ ከእግዚአብሔር መለየት። ንስሀ በመግባት እና ትእዛዛትን በማክበር ከመንፈሳዊ ሞት በኢየሱስ ክርስቶስ የኃጢያት ክፍያ እንድናለን።

**መንፈስ** ከመወለድ በፊት ከሰማይ አባት ጋር ይኖር የነበረ የሰው አካል። በምድር ህይወት ጊዜ፣ መንፈስ ከስጋዊ ሰውነት ጋር ይገጣጠማል። ከሞት በኋላ መንፈስ በመኖር ይቀጥላል።

**ስነስርዓት** በክህነት ስልጣን የሚከናወን ቅዱስ፣ መደበኛ ስራ። ምሳሌዎችም በተጨማሪ ጥምቀት፣ ቅዱስ መንፈስን መቀበል፣ እናም ቅዱስ ቁርባን ናቸው። ስነስርዓቶች ከእግዚአብሔር ጋር ቃል የሚገባበት መንገድ ነው።

**ስጋዊ ሞት** መንፈስ ከሟች ሰውነት ጋር መለያየት። ስጋዊ ሰውነት ሲሞት፣ መንፈስ በመንፈስ አለም በመኖር ይቀጥላል። ስጋዊ ሰውነትን በትንሳኤ ለማሸነፍ እንችላለን፣ ይህም የተቻለው በኢየሱስ ክርስቶስ የኃጢያት ክፍያ ነው።

**ቅድመ-ምድር ህይወት** በእዚህ ምድር ላይ ከመወለዳችን በፊት የነበረን ህይወት። በቅድመ-ምድር ህይወታችን፣ በሰማይ አባታችንን ፊት እንደ መንፈስ ልጆቹ እንኖር ነበር። ስጋዊ ሰውነቶች አልነበረንም።

**ትንሳኤ** ከስጋዊ ሞት በኋላ፣ መንፈስ ፍጹም ከሆነ ስጋ እና አጥንት ያለው ስጋዊ ሰውነት ጋር በዳግም የሚገናኝበት። በመጀመሪያ ከሞት የተነሳው ኢየሱስ ክርስቶስ ነበር። ከትንሳኤ በኋላ፣ መንፈስ እና ሰውነት እንደገናም አይለያዩም፣ እናም ሰውም ለዘለአለም ይኖራል። ይኖር የነበረው ሰው ሁሉ በኃጢያት ክፍያ ምክያት ከሞት ይነሳል።

**ነጻ ምርጫ** በመልካም እና በክፉ መካከል፣ በትክክል እና ትክክል ባልሆነው መካከል ለመምረጥ ከእግዚአብሔር የመጣ ስጦታ።

**ውድቀት** የሰው ዘር ስጋዊ የሆነበት ሁኔታ። ይህም ከእግዚአብሔር በመንፈስ እና በስጋ መለያየትን አመጣ። የመጀመሪያው ሰዎች፣ አዳም እና ሔዋን የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ስለተላለፉ፣ ከፊቱ ተለይተው ነበር (ይህም መለየት የመንፈስ ሞት ተብሎ ይጠራል) እናም ስጋዊ (ለስጋዊ ሞት ተገዢ) ሆነዋል። እንደ አዳም እና ሔዋን ትውልዶች፣ እኛ ደግሞም ከእግዚአብሔር ተለይተናል እናም በስጋዊ ሞት ተገዢ ነን። የኢየሱስ ክርስቶስ የኃጢያት ክፍያ ስጋዊ እና መንፈሳዊ ሞትን ያሸንፋል።

**የመንፈስ አለም** በሞት እና በትንሳኤ መካከል መንፈሳችን የሚሄዱበት ቦታ። በህይወታቸው ጻድቅ ለሆኑት፣ የመንፈስ አለም የሰላም እና የደስታ ቦታ ይሆናል።

**የኃጢያት ክፍያ** ከእግዚአብሔር ጋር እንድንታረቅ ያስቻለን ድርጊት። ለኃጢያት መክፈል ማለት ለኃጢያት ቅጣት መሰቃየት ነው፣ በእዚህም የኃጢያትን ውጤት ንስሀ ከሚገባው ኃጢያተኞች ያስነሳል። ለሰው ዘር ሁሉ ፍጹም የሆነ የኃቲያት ክፍያ ማድረግ የሚችለው ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነበር። የኃጢያት ክፍያውም በተጨማሪ ለኃጢያቶቻችን መሰቃየት፣ የደሙ መፍሰስ፣ እና ሞቱና ትንሳኤው ናቸው። በኃጢያት ክፍያ ምክን ያት፣ ይኖር የነበረው እያንዳንዱ ሰው ከሞት ይነሳል። የኃጢያት ክፍያም ለኃጢያታችን ምህረት ለማግኘት እና ከእግዚአብሔር ጋር ለዘለአለም ለመኖር የሚያስችለን መንገር ይሰጠናል።

**የደህንነት እቅድ** እንደ እርሱ እንድንሆን እና የደስታ ሙላትን ለመቀ በል እንድንችል የሰማይ አባት የሰራው ዓላማ። በኢየሱስ ክርስቶስ የኃጢያት ክፍያ ላይ የተመሰረተ ነው እናም በተጨማሪ ትእዛዛት፣ ስነስርዓቶች፣ እና የወንጌል ትምህርቶች ናቸው።

**ደህንነት** ከኃጢያት እና ከሞት መዳን። ደህንነት የሚቻለው በኢየሱስ ክርስቶስ የኃጢያት ክፍያ በኩል ነው። በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሳኤ በኩል፣ እያንዳንዱም የሞት ውጤትንያሸንፋሉ። በኢየሱስ ክርስቶስ እምነት በኩልም ከኃጢያት ውጤቶች ለመዳን እንችላለን። ይህም እምነት ንስሀ በሚያገባ እና በወንጌል ህግጋት እና ስነስርዓቶች ታዛዥ በሆነ ህይወት እና ክርስቶስን በማገልገል ይገለጻል።

**ጸጋ** በኢየሱስ ክርስቶስ ምህረት እና ፍቅር በኩል የሚሰጥ መለኮታዊ እርዳታ እና ጥንካሬ። በኃጢያት ክፍያው እንዲቻል ባደረገው በእርሱ ጸጋ በኩል፣ የሰው ዘር በሙሉ ከሞት ይነሳሉ። በእርሱ ጸጋ በኩል፣ ሁልጊዜው ንስሀ የሚገቡ እና በወንጌሉ መሰረት የሚኖሩ በእዚህ ህይወት ከሰማይ አባት ጋር የሚጸና ቅርብነት ይሰማቸውል እና ከእዚህ ህይወት በኋላም በእርሱ ፊት ይኖራሉ።

## በተጨማሪ የሚጠኑ

**የሚቀጥሉት ጥያቄዎች እና ቅዱሳት መጻህፍት በእዚህ እትሞች ውስጥ ስለሚገኙት መሰረታዊ መመሪያዎች በተጨማሪ ለመማር እና እንድታሰላስሏቸው ይረዱችኋል። ዝርዝሩ ኍሉንም የሚሸፍኑ አይደሉም፤ በቅዱሳት መጻህፍት ውስጥ ያሉ የግርጌ ማስታወሻዎች እና ማጣቀሻዎች ወደ ተጨማሪ ፅሁፎች ይመሯችኋል።**

**ከመወለዳችሁ በፊት ከእግዚአብሔር ጋር ምን ግንኙነት አላችሁ?**

ኤርምያስ 1፥5 (መፅሐፍ ቅዱስ፣ ብሉይ ኪዳን)

ዕብራውያን 12፥9 (መፅሐፍ ቅዱስ፣ ብሉይ ኪዳን)

---

---

---

**ውድቀት ምንድን ነው? ለምን አስፈላጊ ነበር?**

2 ኔፊ 2፥14–26 (መፅሐፈ ሞርሞን፣ ገፅ 45-46)

አልማ 42፥2–9 (መፅሐፈ ሞርሞን፣ ገፅ 260)

---

---

---

**የእዚህ ህይወታችሁ እቅድ ምንድን ነው? ይህን ማወቅ እንዴት የቀን በቀን ውሳኔአችሁ ላይ ተፅዕኖ አለው?**

2 ኔፊ 2፥25–27 (መፅሐፈ ሞርሞን፣ ገፅ 46)

አልማ 34፥32 (መፅሐፈ ሞርሞን፣ ገፅ 246)

---

---

---

**የኃጢያት ክፍያ ምንድን ነው? በቀን የቀን ህይወታችሁ ይህ እን ዴት ሊረዳችሁ ይችላል?**

የሀንስ 3፥16–17 (*መፅሐፍ ቅዱስ፣ አዲስ ኪዳን*)

ሮሜ 3፥23–25 (*መፅሐፍ ቅዱስ፣ አዲስ ኪዳን*)

2 ኔፊ 2፥6–8 (*መፅሐፈ ሞርሞን፣ ገፅ* 45)

አልማ 7፥11–12 (*መፅሐፈ ሞርሞን፣ ገፅ* 183-184)

አልማ 42፥22–23 (*መፅሐፈ ሞርሞን፣ ገፅ* 261)

**የአለም መንፈስ ምንድን ነው? በእዚያ ምን ደረሰ?**

1 ጴጥሮስ 4፥6 (*መፅሐፍ ቅዱስ፣ አዲስ ኪዳን*)

አልማ 40፥11–14 (*መፅሐፈ ሞርሞን፣ ገፅ* 257)

**ትንሳኤ ምን ማለት ነው? ከሞት ማን ይነሳል? ትንሳኤ ለምን አስፈላጊ ነው?**

2 ኔፊ 9፥13–15 (*መፅሐፈ ሞርሞን፣ ገፅ* 57-58)


አልማ 11፥42–45 (*መፅሐፈ ሞርሞን፣ ገፅ* 194)

**ሰማይ ምንድን ነው? የተለያዩ የክብር ደረጃዎች ለምን አሉ?**

1 ቆሮንጦስ 15፥40–43 (*መፅሐፍ ቅዱስ፣ አዲስ ኪዳን*)

# ከእኛ ጋር አብራችሁ አምልኩ

### በዳግም የተመለሰው ወንጌል እንዴት ህይወታችሁን እንደሚባርክ ኑ እና ተመልከቱ



የቅዱስ ቁርባን ስብሰባ ዋናው አምልኮ አገልግሎት ነው። ይህም ከአንድ ሰዓት በትንሽ የሚያልፍ እና በልምድ የሚከተሉት የሚገኝበት ነው፥

*መዝሙሮች፥* በተሰበሰቡት የሚዘመር። (የመዝሙር መፅሐፎች ይሰጣሉ።)

*ጸሎቶች፥* በአካባቢው አባል በሆኑት የሚቀርብ።

*ቅዱስ ቁርባን፥* ዳቦ እና ውሀ ይባረካሉ እና የኢየሱስ ክርስቶስ የኃጢያት ክፋን ለማስታወስ በተሰበሰቡት መካከል ይተላለፋል።

*ንግግር አቅራቢዎች፥* በልምድ ከእዚህ በፊት የተመደቡ ከተሰበሰቡት አባላት አንድ ወይም ሁለት ሰዎች ስለወንጌል ርዕስ ንግግር ያቀርባሉ።

*ልብሶች፥* ወንዶች በአጠቃላይ ሱፍ ወይም ጥሩ ሱሪ ከሸሚዝና ከከረባት ጋር ይለብሳሉ። ሴቶችት ቀሚሶችን ይለብሳሉ።

በአምልኮ አገልግሎት ጊዜ ምፅዋት አይጠየቅም።

በእድሜአችሁ እና ግላጎት ባላችሁ ነገሮች ላይ የሚመሰረቱ ተጨማሪ ስብሰባዎችን እንድትሳተፉበት እንጠይቃችኋለን። የእነዚህ ስብሰባዎች ቅድመ ተከተል እና መገኘት ከቦታ ወደቦታ ይለያያል።

*የሰንበት ትምህርት ቤት፥* ቅዱሳት መጻህፍት እና የወንጌል ትምህርቶች የሚጠኑበት ክፍሎች።

*የክህነት ስብሰባዎች፥* 12 እና ከእዚያ በላይ ለሆኑ ወንዶ ያለ ክፍል።

*የሴቶች መረዳጃ ማህበር፥* ለ18 እና ከእዚያ በላይ ለሆኑ ሴቶች ያለ ክፍል።

*ወጣት ሴቶች፥* ከ12 እስከ 18 አመት ለሚሆኑ ሴቶች ያለ ክፍል።

*የመጀመሪያ ክፍል፥* ከ3 እስከ 11 አመት ለሆኑ ልጆች ያለ የቡድን አገልግሎት እና ክፍሎች። ከ18 ወራት እስከ 3 አመት ለሆኑ ልጆች ያለ የህጻናት መንከባከ ቢያ ቦታም በብዙ ጊዜ ይገኛል።



የቅዱስ ቁርባን ስብሰባ ሰዓት፥ ____________________

የቤተክርስቲያን አድራሻ፥ ____________________

____________________

____________________




## ምን ማድረግ ይገባኛል?

- መፅሐፈ ሞርሞንን አንብቡ።
  ለማንበብ የሚገባበትን የሚያቀርብ ሀሳብ፥ __________

- የወንጌል መልእክተኞች ያስተማሯችሁ እውነት እንደሆኑ ለማወቅ ጸልዩ።
- በቤተክርስቲያን ተሳታፊ ሁኑ።
- በ ____________________ ቀን ለመጠመቅ ተዘጋጁ።
- የሰማይ አባል ለልጆቹ ስላለው እቅድ በተጨማሪ ለመማር www.mormon.org ተመልከቱ።
- በእዚህ ዘመን ነቢያት በኩል እግዚአብሔር በዳግም ስለመለሳቸው እውነቶች በተጨማሪ ለመማር ከወንጌል መልእክተኞች ጋር በመገናኘት ቀጥሉ።

  የሚቀጥለው ቀጠሮ፥ ____________________

  የወንጌል መልእክተኞች ስም እና የስልክ ቁጥሮች፥

የኋለኛው ቀን ቅዱሳን
የኢየሱስ ክርስቶስ
ቤተክርስቲያን

www.mormon.org

ለስዕል ምስጋናዎች
የፊትለፊት መሸፈኛው፥ *ተነስቷል፤* የሚለውን ከሚዘረዝረው፤ በዳል ፓርሰን። © Del Parson. ግልባጭ አትስሩ
ገፅ 11: *ክርስቶስ በገትሰመኔ* የሚለውን ከሚዘረዝረው፤ በሀሪ አንደርሰን
ገፅ 13: *ተነስቷል፤* በግሬግ ኦልሰን © Greg Olsen ግልባጭ አትስሩ

© 2011 በIntellectual Reserve, Inc. መብቶቹ በህግ የተጠበቁ። በዩኤስኤ ውስጥ የታተመ።
እንግሊዘኛው የተፈቀደበት: 8/08። ትርጉን የተፈቀደበት: 11/05. *The Plan of Salvation* ትርጉም።
Amharic. 01197 506

AMHARIC
4 02011 97506 1
01197 506